የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Trade & Industry

# የወጪ ምርቶች ውል ምዝገባና አፈፃፀም

## መመሪያ ቁጥር 560/2013

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

ጥቅምት 2012 ዓ.ም

## የወጪ ምርቶች ውል ምዝገባና አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 560/2013

የወጪ ምርቶቻችን ንግድ ውስጥ የሚፈጸሙ ውሎችን ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለው የውል ምዝገባና አፈጸፀም ስርዓትን በመዘርጋት የአገራችንን የውል አተገባበር መልካም ገጽታን በመገንባት ምርቶቻችን በውጭ ገበያ ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በወጪ ምርቶቻችን ሽያጭ ላይ የሚፈጸሙ የወጪ ንግድ ውሎችን ባለመፈፀም በተዋዋይ ወገኖች እና በሀገር መልካም የውል አተገባበር ገጽታ ጉዳት በሚያደርሱ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ ሀገራዊ መልካም ገጽታን መገንባት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

አላግባብ ለረጅም ጊዜ በክምችት የሚያዙ የወጪ ምርቶች በወቅቱ ተልከው ለአገሪቱ ሊገኝ የሚችለውን የውጭ ምንዛሬ ገቢ በወቅቱ ማስገኘት በማስፈለጉ፤

የወጪ ምርቶች ግብይትን ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት የተዋዋይ ወገኖችን እና ሀገራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ በማስፈለጉ፤

የኢ.ፌ.ድ.ሪ የፌደራል አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀፅ 19(1-መ) መሠረት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1) **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ ‹‹**የወጪ ምርቶች ውል ምዝገባና አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር** 560/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2) **የቃላት ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር፣ በዚህ መመሪያ፡-

1. ‹‹**የወጪ ምርቶች ውል**›› ማለት በወጪ ምርቶች ላይ በላኪዎች (ሻጭ) እና ውጭ ሀገር በሚገኙ ገዥዎች መካከል የሚፈጸም ውል ነው፤
2. ‹‹**የወጪ ምርቶች ውል ምዝገባ**›› ማለት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም ሌላ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚከናወን በአገራችን ላኪዎች (ሻጭ) እና ውጭ ሀገር በሚገኙ



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

ገዥዎች መካከል የሚፈጸም ውልን በዚህ መመሪያ የተጠቀሱት መስፈርቶች ማሟላቱን በማረጋገጥ የሚደረግ ምዝገባና የሚሰጥ የምዝገባ ማረጋገጫ ነው፤

3. **‹‹የወጪ ምርቶች ውል አፈፃፀም ክትትል››** ማለት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዚህ መመሪያ መሠረት መዝግቦ ማረጋገጫ የሠጣቸው ውሎች ስለመፈፀማቸው በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም ሥልጣን በተሰጠው ሌላ አካል የሚደረግ የክትትል ስርዓት ነው፤

4. **‹‹የግብይት ተዋናይ››** ማለት የወጪ ምርቶችን ወደ ውጭ ሀገር የሚልኩ እና በውጭ ሀገር የሚገኙ የሀገራችንን የወጪ ምርቶችን የሚገዙ ማናቸውም ሰዎች ናቸው፤

5. **‹‹የወጪ ምርት ላኪዎች››** ማለት የወጪ ምርቶችን ወደውጭ ለመላክ ውል የሚፈጽሙ በመስኩ የፀና የላኪነት ፈቃድ ያላቸው፣ በማሳቸው ያመረቱትን እንዲልኩ በሕግ መብት የተሰጣቸው ወይም የሕብረት ስራ ማኅበራት ናቸው፤

6. **‹‹ገዥ››** ማለት በውጭ ሀገር የሚገኙና የወጪ ምርቶችን የሚገዙ ማናቸውም ሰዎች ናቸው፤

7. **‹‹የምዝገባ ማመልከቻ››** ማለት የወጪ ምርቶችን ውጭ ሀገር ለሚገኙ ገዥዎች ለመላክ የገቧቸውን ውሎች ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም ሥልጣን ለተሰጠው ሌላ አካል በላኪዎች ለምዝገባ የሚቀርብ ማመልከቻ ነው፤

8. **‹‹የወጪ ምርቶችን በክምችት በመያዝ የሚገባ ውል››** ማለት ላኪው ወደውጭ ለመላክ ውል ሲገባ ምርቱ ሙሉ ለሙሉ በክምችት የሚገኝ ሲሆን ነው፤

9. **‹‹የወጪ ምርቶች በክምችት ሳይያዝ የሚገባ ውል››** ማለት ላኪው ምርቱን በክምችት ሳይዝ ውጭ ሀገር ከሚገኘው ገገር ጋር ምርትን ወደውጭ ለመላክ በቅድሚያ የሚገባ የሽያጭ ውል ነው፤

10. **‹‹የአገር ውስጥ ገበያ የግዢ ዋጋ››** ማለት ላኪው ምርቱን ከአገር ውስጥ ገበያ የገዛበት ዋጋ ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት በተለያየ ዋጋ የተገዙ ምርቶች በአንድ ውል ሲላኩ አማካይ የግዢ ዋጋቸው የአገር ውስጥ ገበያ የግዢ ዋጋ ነው ተብሎ ይታሰባል፤

11. **‹‹ከውጭ ገበያ ዋጋ በላይ መግዛት››** ማለት ከውጭ ገበያ ዕለታዊ አማካይ ዋጋ በላይ ሆን ተብሎ ዋጋን በማናርና የግብይት ሥርዓቱን በማዛባት ከአገር ውስጥ ገበያ የሚፈጸም ግዢ ነው፤

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

12. **‹‹ከአገር ውስጥ ገበያ ዋጋ በታች መሸጥ››** ማለት የወጪ ምርቶችን በውጭ ገበያ ላይ በአገር ውስጥ ገበያ ከተገዙበት ዋጋ ወይም ከማነፃፀሪያ ዋጋ በማሳነስ መሸጥ ማለት ነው፤

13. **‹‹የወጪ ምርቶቻችን በውጭ ገበያ የመሸጫ ዋጋን ማነፃፀር››** ማለት የወጪ ምርቶች በውጭ ገበያ ላይ በየዕለቱ የሚሸጡበት ዋጋን አለም አቀፋዊ ታዓማኒነት ያላቸው የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሞ የወጪ ምርትን የዕለቱን የውጭ ገበያ ዋጋን ከአገር ውስጥ ገበያ ጋር በንጽጽር የማሳወቅ ሂደት ነው፤

14. **‹‹የወጪ ምርቶች ዋጋ ጥናት ቡድን››** ማለት የወጪ ምርቶችን የአገር ውስጥ ገበያ ዕለታዊ መሸጫ ዋጋንና የውጭ ገበያ ዋጋን መሠረት በማድረግ ማነፃፀሪያ ዋጋ የሚያዘጋጅ፣ በወጪ ምርቶች ዋጋ ዙሪያ ጥናት የሚያካሂድ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚቋቋም የወጪ ምርቶች ዋጋ ጥናት ቡድን ማለት ነው፤

15. **‹‹የወጪ ምርቶች ዋጋ ጥናት አማካሪ ቦርድ››** ማለት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን የወጪ ምርቶች ዋጋ ጥናት ቡድን የሚያማክር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ አማካሪ ቦርድ ማለት ነው፤

16. **‹‹ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ››** ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፤

17. **‹‹ባለድርሻ አካላት››** ማለት የግብርና ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና የንግድ ባንኮች፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የዘርፍ ማኅበራት እና የብቃት አረጋጋጭ አካላት ማለት ነው፤

18. **‹‹አስተዳደራዊ እርምጃ››** ማለት የወጪ ምርቶች በሚልኩ ማንኛውም ላኪዎች ላይ የንግድ ስራ ፈቃድን ማገድ፣ መሰረዝ፣ የማነፃፀሪያ ዋጋን መነሻ በማድረግ ውሎች እንዲሻሻሉ ማድረግ፣ የሀገሪቱን መልካም የውል አፈጻጸም ገጽታ ለመጠበቅ ሲባል የተገቡ ውሎች በሌሎች ሰዎች እንዲፈጸሙ ማድረግ እና የመሳሰሉት ናቸው፤

19. **‹‹ሰው››** ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ናቸው፤

20. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴት ፆታም ያገለግላል።

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ ማናቸውም የወጪ ምርቶችን ወደውጭ አገር ለመላክ የሚገቡ ውሎችና የእነዚህ ምርቶች ላኪዎች ላይ ተፈጻሚ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በመነሻነት የዚህ መመሪያ አፈፃፀም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የግብይት ሥርዓታቸው በሚፈጸም ምርቶች ላይ ሲሆን ሌሎች የወጪ ንግድ ምርቶች ላይ የሚኖረው አፈፃፀም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚዘረጋው አሠራር መሠረት እየተካተቱ የሚፈጸም ይሆናል፡፡
3. የቡና ምርትን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ጋር በጋራ በሚዘረጋው ሥርዓት በዚህ መመሪያ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# <u>ውልን ስለመመዝገብ</u>

## 4. መመዝገብ ያለባቸው ውሎች

የዚህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው የወጪ ምርቶችን ወደውጭ ለመላክ የሚገቡ ውሎች፣ ለውጦች ወይም መሰረዝ/መቋረጥ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚዘረጋው አሠራር ወይም የኢንፎርሜሽን ግንኙነት ቴክኖሎጂን በመጠቀም በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ የመመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

## 5. ለውል ምዝገባ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአገሪቱን የወጪ ንግድ ምርቶች ውሎች በሙሉ የተቀመጠውን መሥፈርት ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ይመዘግባል፣ የምዝገባ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
2. ለምዝገባ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ሰነዶች አሟልቶ ማቅረብ አለበት፤

   ሀ) የተፈረመና ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት ከተያያዘው ሞዴል ውል ውስጥ የተካተቱን የውል ይዘቶች የሚያሟላ የሽያጭ ውል፣ እና

   ለ) ማመልከቻው የቀረበው በላኪ (ሻጭ) ወኪል ከሆነ ሰነድን በሕግ ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የውክልና ማስረጃ እና የፀና መታወቂያ፡፡

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የወጪ ምርት ውል (Export Contract) እንዲመዘገብ ሲቀርብ ምርቱ ከአገር ውስጥ ገበያ ተገዝቶ በክምችት የተያዘ ከሆነ የግዢ ደረሰኝ ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

4. ምርት ሳይገዛ ለሚመጣ ሻጭ የአገር ውስጥ ገበያ የግዢ ደረሰኝ ሳያቀርብ ነገር ግን የማነፃፀሪያ ዋጋን ባመጣጠነ መልኩ ውሉ ይመዘገብለታል፡፡ ሆኖም ግን ምርቱን ከገዛ በኋላ አዘጋጅቶ ወደውጭ ከመላኩ በፊት የአገር ውስጥ ገበያ የግዢ ደረሠኝን በማቅረብ የተመዘገበው የውል ዋጋ ከአገር ውስጥ ገበያ የግዢ ዋጋ እኩል ወይም የበለጠ መሆኑ እየተረጋገጠ የምዝገባ ማረጋገጫ ይሰጠዋል፡፡

5. የቀረበው ማመልከቻ የውል ማሻሻያ ከሆነ የተመዘገበውን የውል ቁጥር እና የምዝገባ ቀን የያዘ፣ የተዋዋይ ወገኖችን ስም፣ አድራሻ (ስልክን ጨምሮ)፣ እና የፈራሚዎችን ችሎታ (ሥራ አስኪያጅ/ሕጋዊ ወኪል) የያዘ እና ከዋናው ውል ውስጥ የተሻሻለውን የውል ድንጋጌ በግልጽ የሚያሳይ በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 6. የወጪ ምርቶች ሽያጭ ውል አመዘጋገብ ሥርዓት

1. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በየዕለቱ በአገር ውስጥ የሚከናወነውን ግብይት በየድርጅት ስም በመረጃ ቋት ይይዛል፡፡

2. ምርት በክምችት በመያዝ የሚከናወን የወጪ ምርት ውልን ስለመመዝገብ

   ሀ) ለምዝገባ ማመልከቻ ያቀረበው አመልካች ምርቱን ከአገር ውስጥ ገበያ ገዝቶ ምርቱ በክምችት የሚገኝ ሲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አመልካቹ የገዛበት አማካይ ዋጋ እና ልዩ ልዩ ወጪዎችን በማካተት በዕለቱ የአሜሪካን ዶላር የባንኮች መግዣ ዋጋ መሠረት አስልቶ አመልካቹ ከሸጠበት ዋጋ ጋር አነፃፅሮ **የውሉ የሽያጭ ዋጋ ከጠቅላላው የግዢ ዋጋ ጋር እኩል ወይም በላይ** ሲሆን ውሉን ይመዘግባል፣ የምዝገባም ማረጋገጫ ለአመልካቹ ይሰጣል፡፡

   ለ) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ማረጋገጫ ከመስጠቱ በፊት አመልካች (ሻጭ) ይዞት የመጣውን የአገር ውስጥ ገበያ የግዢ ደረሰኝ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የግዢ የመረጃ ቋት ጋር በትክክል በማመሳከር ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የገዛውን ምርት



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

በሺያጭ ውሉ መሠረት በሚያቀርበው ደረሰኝ ላይ እና በመረጃ ቋት ውስጥ ካለው የግገር መረጃ ላይ ማቀናነስ ይኖርበታል፡፡

ሐ) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምርት በመያዝ ውሉን ለማስመዝገብ የመጣን አመልካች ሌሎች መስፈርቶችን ማሟላቱን በማረጋገጥ ውሉን መመዝገብ እና የምዝገባ ማረጋገጫ ወዲያውኑ መስጠት ይኖርበታል፡፡

3. ምርት ሳይኖር ለሚከናወን የወጪ ምርት ውልን ስለመመዝገብ

ሀ) የወጪ ምርት ውል በክምችት ሳይኖረው የተገባ ውል ከሆነ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የውሉን ዋጋ ከማነፃፀሪያ ዋጋ ያላነሰ መሆኑንና የወጪ ምርት ውል መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን እንዲሁም የውሉ የማቅረቢያ ጊዜ (Shipment Period) ከ3 ወር ያልበለጠ መሆኑን በማረጋገጥ ውሉን ይመዘግባል፡፡

ለ) በዚህ መመሪያ መሠረት ምርት ሳይኖር ለሚመዘገብ የወጪ ምርት ውል የምዝገባ ማረጋገጫ የሚሰጠው ምርቱን ገዝቶ ካቀነባበረ እና ለጭነት ዝግጁ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

ሐ) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምርት ሳይኖረዉ ለመዘገበዉ የወጪ ምርት ውል የምዝገባ ማረጋገጫ የሚሰጠው አመልካች (ሻጭ) የገዛበትን የአገር ውስጥ ገበያ ደረሰኝ በማየት የተመዘገበዉ የወጪ ምርት ዉል የመሸጫ ዋጋ እና ከአገር ውስጥ ገበያ የገዛበት አማካይ ዋጋ ከልዩ ልዩ ወጭዎች ጋር ተደምሮ እኩል መሆኑን ወይንም የበለጠ መሆኑን እና የጭነት ጊዜዉ ከተጠቀመጠለት ጊዜ በላይ አለማለፉን በማረጋገጥ ነው፡፡

መ) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከአገር ውስጥ ገበያ ያገኘዉን የግዥ መረጃ እና አመልካች (ሻጭ) ይዞት የመጣዉን ደረሰኝ በማመሳከር ማቀናነስ አለበት፡፡

ሠ) ማንኛውም የወጪ ምርት ውል በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያላሟላ መሆኑ ሲረጋገጥ ምዝገባ አይከናወንም፣ የምዝገባ ማረጋገጫም አይሰጥም፡፡

## 7. የአምራቾች፣ የሕብረት ሥራ ማኅበራት ወይም ቀጥታ ላኪዎች ውል ምዝገባ

በአገር ውስጥ ገበያ ወይም የግብይት ማዕከላት በኩል ሳያልፉ በቀጥታ ምርትን ወደውጭ እንዲልኩ በሕግ የተፈቀደላቸው ቀጥታ ላኪዎች የሚያቀርቡት የወጪ ምርት ውል በዚህ መመሪያ መሠረት በሚወሰነው የዋጋ ማነፃፀሪያ እኩል ወይም የበለጠ ሆኖ ሲገኝ እና



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(2) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ የሚመዘገብና የምዝገባ ማረጋገጫ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

## 8. የዕለታዊ የአገር ውስጥ ገበያ ሽያጭና የመሸጫ ዋጋ ማነፃፀር

1. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምርት በክምችት ሳይኖረው ወይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት የተገባ ውል ዋጋን ለመወሰን በየዕለቱ ማነፃፀሪያ የሚሆነውን በውጭ ገበያ መሸጫ ዋጋ የተለያዩ አስተማማኝ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀምና በየእለቱም ዋጋውን በማስላት እና ከአገር ውስጥ የገበያ ዋጋ ጋር በማነፃፀር የምርቶችን ወደውጭ መላኪያ የገበያ ማነፃፀሪያ ዋጋን ይወስናል፡፡
2. የአገር ውስጥ ገበያ ማዕከላት አካላት በማዕከላቸው የሚከናወኑ ግብይቶችን በየዕለቱ የገገር ድርጅቶችን ማንነትና የገዙት መጠንና ዋጋ የያዘ መረጃ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወዲያውኑ ያሳውቃሉ፡፡
3. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የየዕለቱን የአገር ውስጥ ገበያ ዋጋን ግገር ጤናማነት ለማረጋገጥ በዕለቱ ከአገር ውስጥ የገበያ ማዕከላት የተላከለትን የገገር ዝርዝር በመመልከት ከዕለቱ የዓለምአቀፍ ዋጋ በላይ የገዙ ኩባያዎችን በነጋታው በአገር ውስጥ ገበያ ግብይት ላይ እንዳይሳተፉ አግዶ የምርት ርክክብ እንዳይካሄድ ያደርጋል፡፡
4. ማንኛዉም የወጪ ምርት ውል በተቻለ መጠነ ከማነፃፀሪያ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር እኩል ወይም የበለጠ መሆን ይገባዋል፡፡ ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈቀድ ምክንያታዊ ምዝገባ (Tolerance Rate) ከ1% መብለጥ የለበትም፡፡

## 9. የምዝገባ ማመልከቻ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ

1. አመልካቹ ለወጪ ምርት ውል ምዝገባ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በትክክል ሞልቶ ከላይ በአንቀጽ 5 እና 6 ከተጠቀሱት ሰነዶች ጋር በማያያዝ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ማመልከቻውን ተቀብሎ የማመልከቻ ቅፁ በትክክል መሞላቱን፣ ሰነዶችና መስፈርቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡
3. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መስፈርቶቹን የሚያሟላ የወጪ ምርት ውልን ልዩ የምዝገባ ቁጥር ሰጥቶ ለአመልካቹ በግማሽ ሰዓት (30 ደቂቃ) ውስጥ የምዝገባ ማረጋገጫ ይሰጠዋል፣ ውሉን ያጸድቃል፡፡ አስፈላጊውን መስፈርት የማያሟሉ ማመልከቻዎችን መሟላት

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

ያለባቸውን ሁኔታዎች በማስረዳት እና የምክር አገልግሎት በመስጠት አመልካቹን ያስተናግዳል፡፡

### 10. የመመዝገብ ውጤት

የተመዘገበ የሽያጭ ውልን ለባንክ በማቅረብ አስፈላጊውን ምርትን ወደውጭ የመላክ ሂደት ውስጥ የሚጠየቁ የባንክ/የጉምሩክ መስፈርቶችን አሟልቶ ምርቱን ወደውጭ ለመላክ ያስችለዋል፡፡ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያልተመዘገበ የወጪ ንግድ ሽያጭ ውል ምርትን ወደውጭ ለመላክ አያስችልም፤ ውጤትም አይኖረውም፡፡

### 11. የውል ማሻሻያዎች እና ማቋረጫዎች

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተመዘገቡ ውሎች ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች ወይም በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረሰበት ውል ማቋረጥ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቀርቦ ውሉ በተመዘገበበት ተመሳሳይ ሁኔታ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ በዚህ ሁኔታ ያልተመዘገበና በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የምዝገባ ማረጋገጫ ያልተሠጠው ማሻሻያ ወይም የውል ማቋረጫ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

### 12. ባለድርሻ አካላትን ማሳወቅ

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መስፈርቶችን ለሚያሟላ የወጪ ምርት ውል የምዝገባ ማረጋገጫ ሲሰጥ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በግልባጭ ያሳውቃል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

### 13. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

1. የወጪ ምርቶች ውል ምዝገባና አፈፃፀም ክትትልን እንዲሁም የዋጋ ጥናት ቡድንን ያደራጃል፤ አስፈላጊ ግብዓቶችንም ያሟላል፤
2. የወጪ ምርቶች ውል ምዝገባን ያከናውናል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤
3. የወጪ ምርቶች የዋጋ ጥናት አማካሪ ቦርድን ይሰይማል፤

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry Archives
መዝገብ ቤት

4. የወጪ ምርቶች የአገር ውስጥ ገበያ ዋጋን እና የአለም ገበያ ዋጋን መሠረት በማድረግ የሚወሰነው የማነፃፀሪያ ዋጋ ለግብይት ተዋንያን ተደራሽ በሆኑ የመገናኛ ብዙሀን አውታሮችም ያሳውቃል፤

5. ከማነፃፀሪያ ዋጋ በላይ አጋነው ከአገር ውስጥ ገበያ ግገር በሚፈጽሙ ወይም ከአለም አቀፍ የመሸጫ ዋጋ አሳንሰው በሚሸጡ ወይም እንደውል በማይፈጽሙ ሰዎች ወይም በማንኛውም መልኩ ይህን መመሪያ ተላልፈው በሚገኙ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ እንደውሉም እንዲፈጸም ያደርጋል፤

6. የተገቡ ውሎችን በማስፈጸም የአገሪቱን መልካም የውል አፈጻፀም ገጽታ ለመጠበቅ ሲባል በሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙበትን ሁኔታ ያፈላልጋል፤

7. የወጪ ምርቶቻችንን ውል በመፈጸም እና በመግዛት እንደውል በማይፈጽሙ የውጭ ሀገራት ገዥዎች እንደውል እንዲፈጽሙ ለማድረግ በዲፕሎማቲክ ግንኙነት መስመሮች ወይም በሌሎች አመቺ ሁኔታዎች ሁሉ ጥረት ያደርጋል፣ እንደውል ላልተፈጸመላቸው ላኪዎች (ሰዎች) አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

8. በዚህ መመሪያ የሚሸፈኑ የወጪ ምርቶች እንደውል የማይፈጽሙ ተዋዋይ ወገኖች በጋራ መግባባት ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ መድረክ ያመቻቻል፤

9. በመስኩ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ያከናውናል፤

10. ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን በጉዳዩ ላይ ያስተባብራል፤

11. ለዚህ መመሪያ አፈጻፀም የሚያግዙ እና የወጪ ንግድን ለማስፋፋት የሚያግዙ ማንኛውንም ተግባራት ያከናውናል፣ እና

12. ለዚህ መመሪያ አፈጻፀም የሚያግዙ ማሻሻያዎችን ያወጣል፡፡

## 14. የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ንግድ ባንኮች ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) ለላኪዎች በባንኮቹ የሚሰጠው አገልግሎትን የተቀላጠፈ፣ ፈጣንና ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፤

ለ) የንግድ ባንኮች በዚህ መመሪያ የሚሸፈኑ የወጪ ምርቶች ውል በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም ሥልጣን በተሰሠጠው ሌላ አካል የተመዘገቡ መሆናቸውን በማረጋገጥ ቀጣይ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

ሐ) የወጪ ምርቶች ውልን በተመለከተ ማናቸውንም በእጃቸው የሚገኙ መረጃዎችን በወቅቱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው የኢንፎርሜሽን ግንኙነት ቴክኖሎጂ አማካኝነት ወይም በሚዘረጋው አሠራር መሠረት ያሳውቃል፤

መ) የወጪ ምርቶች የዋጋ ጥናት አማካሪ ቦርድ አባል በመሆን ያገለግላል፣ እና

ሠ) ሌሎችም ለመስኩ ጠቃሚ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይሰራል።

2. **የግብርና ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) በዚህ መመሪያ የሚሸፈኑ የግብርና ምርቶችን አይነትና መጠን በተመረቱበት ስነ-ምህዳር በመለየት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚዘረጋው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወይም አሠራር መሠረት ያሳውቃል፤

ለ) ለቡና ምርት እና ግብርና ሚኒስቴር ክትትል ለሚያደርግባቸው የወጪ ንግድ ምርቶች ይህንን መመሪያ መሠረት በማድረግ የውል ምዝገባ አሠራር ሥርዓት በሥሩ በሚገኙ ተጠሪ ተቋማት እንዲዘረጋ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ሐ) የወጪ ምርቶች የዋጋ ጥናት አማካሪ ቦርድ አባል በመሆን ያገለግላል፣ እና

መ) በዚህ መመሪያ አፈፃፀም ዙሪያ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በትብብር ይሰራል።

3. **የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) ይህንን መመሪያ ተከትሎ ለቡና ምርት የወጪ ውሎች ምዝገባና ክትትልን ያደራጃል፤ አስፈላጊ ግብዓቶችንም ያሟላል፤

ለ) የቡና ምርትን ወደውጭ ለመላክ የሚገቡ ውሎች በዚህ መመሪያ የቀመጡ መስፈርቶችን እንዲሁም እንደምርቱ ባህሪ በዚህ መመሪያ መሠረት በሚዘረጋው የአሠራር ስርዓት መሠረት የሚጠየቁ ሌሎች መስፈርቶች ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የቡና ምርት የወጪ ሽያጭ ውሎችን ይመዘግባል፤ የምዝገባ ማረጋገጫ ይሰጣል፤

ሐ) የመዘገባቸውን ውሎች አፈፃፀም ይከታተላል፣ እና

መ) በዚህ መመሪያ አፈፃፀም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በትብብር ይሰራል።

4. **የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) የየዕለቱን የግብይት መረጃ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይልካል፤



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

ለ) በውል ምዝገባ እና አፈፃፀም ክትትል ላይ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በትብብር ይሰራል፣ እና

ሐ) ሌሎችም ለመስኩ ጠቃሚ የሆኑ ተግባትን ያከናውናል፡፡

5. **የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚከናወኑ ግብይቶችን ጤናማነት ይመረምራል፣ በተለዩ ውጤቶች ላይ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

ለ) የወጪ ምርቶች የዋጋ ጥናት አማካሪ ቦርድ አባል በመሆን ያገለግላል፣ እና

ሐ) ሌሎችም ለመስኩ ጠቃሚ የሆኑ ተግባትን ያከናውናል፡፡

6. **የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) በዚህ መመሪያ የሚሸፈኑ የወጪ ምርቶች ውል በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም ሌላ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተመዘገቡ መሆናቸውን በማረጋገጥ እንዲያልፉ ያደርጋል፤

ለ) የወጪ ምርቶች የዋጋ ጥናት አማካሪ ቦርድ አባል በመሆን ያገለግላል፣ እና

ሐ) የወጪ ምርቶች የላኩ ሰዎች፣ መጠን፣ ዓይነት እና ሌሎችም ጠቃሚ መረጃዎችን በመያዝ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው የኢንፎርሜሽን መገናኛ ዘዴ ወይም በሚዘረጋ አሠራር መሠረት በወቅቱ ያሳውቃል፡፡

7. **ጉዳዩ የሚመለከታቸው የዘርፍ ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) የላኪዎች እንደውል መፈጸም አቅምንና አጠቃላይ በዘርፉ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ያከናውናል፣ እና

ለ) የወጪ ምርቶች የዋጋ ጥናት አማካሪ ቦርድ አባል በመሆን ያገለግላል፡፡

## 15. የወጪ ምርቶች ዋጋ ጥናት ቡድን እና የአማካሪ ቦርድ አደረጃጀት

1. የወጪ ምርቶች ዋጋ ጥናት ቡድን

የተለያዩ አስተማማኝ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም የየእለቱን ዋጋ በመከታተል እና ከአገር ውስጥ የገበያ ዋጋ ጋር በማነፃፀር የወጪ ምርቶችን ወደውጭ መላኪያ የገበያ ማነፃፀሪያ ዋጋ የሚያሰላ እና የሚተነትን እንዲሁም በወጪ ምርቶች ዋጋ ላይ ጥናት

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

የሚያካሄድ የወጪ ምርቶች ዋጋ ጥናት ቡድን በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የንግድ ማስፋፊያ ዘርፍ ሥር ይደራጃል፡፡

2. የወጪ ምርቶች ዋጋ ጥናት ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) የወጪ ምርቶችን የአገር ውስጥ የእለት የገበያ ዋጋን እና ከተለዩ አስተማማኝ የመረጃ ምንጮች የአለም ገበያ ዋጋን ይከታተላል፤

ለ) በየእለቱ በሚገኘው የአገር ውስጥና የአለም ገበያ ዋጋ መሠረት የዋጋ ትንታኔ ይሰራል፣ ማነፃፀሪያ ዋጋም ያዘጋጃል፤

ሐ) በየጊዜው የሚኖረውን የወጪ ምርቶች የገበያ ዋጋ ሁኔታ ያጠናል፣ በጥናት ላይ ተመስርቶ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

መ) አስተማማኝ አለምአቀፍ የገበያ ዋጋ የመረጃ ምንጮችን ይለያል፤

ሠ) የአገር ውስጥ የገበያ ዋጋ ምንጮችን አጣርቶ ለውሳኔ ያቀርባል፤

ረ) የወጪ ምርቶች ከመነሻ እስከ መድረሻ ያላቸውን የግብይት ወጪዎች (logistics costs) ያጠናል፣ ተከታትሎ ወቅታዊ ያደርጋል፣ እና

ረ) ከወጪ ምርቶች ዋጋ ጋር በተያያዘ ዘርፉን ያማክራል፡፡

3. የወጪ ምርቶች ዋጋ ጥናት አማካሪ ቦርድ

የዋጋ ጥናት ቡድኑን የሚያማክር እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ ባለሞያዎችን ያካተተ የወጪ ምርቶች ዋጋ ጥናት አማካሪ ቦርድ ይሰየማል፡፡ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የቦርዱ ሰብሳቢና ጸሀፊ በመሆን የሚከተሉት ተቋማት የሚወከሉባቸው ኃላፊዎች ወይም የዚህ ልዩ ሙያ ያላቸው ባለሙያዎች አባላት የተካተቱበትን ቦርድ ይሰይማል፤

ሀ) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን፣

ለ) የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን፣

ሐ) የግብርና ሚኒስቴር፣

መ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣

ሠ) ጉዳዩ የሚመለከታቸው የዘርፍ ማህበራት፣ እና

ረ) ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚመደቡ ባለሙያዎች፡፡

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

4. የወጪ ምርቶች ዋጋ ጥናት አማካሪ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን የወጪ ምርቶች ዋጋ ጥናት ቡድን ያማክራል፣ እና

ለ) ለመስኩ ጠቃሚ የሆኑ ማናቸውንም ተግባራት ያከናወናል፡፡

## ክፍል አራት

## የግብይት ተዋናይ ተግባርና ኃላፊነት

16. የወጪ ምርቶች ላኪዎች ግዴታ

1. በወጪ ምርቶች ላይ የሚፈጸሙ ውሎችን ወይም የውል ማሻሻያዎችን ወይም የተገባ ውል መቅረትን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ የውል ጉዳዮችን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚዘረጋው አሠራር መሠረት የማስመዝገብ፤
2. በዚህ መመሪያ የሚሸፈኑ ምርቶችን በዚህ መመሪያ መሠረት የወጪ ምርት ውል ዋጋን ከአገር ውስጥ ገበያ ግዢ ወይም ከማነፃፀሪያ እኩል ወይም በላይ የመሸጥ፣
3. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለሚያደርገው የወጪ ምርቶች ውል አፈጻፀም ክትትል የሚያስፈልጉ ወይም የሚጠይቁ መረጃዎችና ማስረጃዎች በወቅቱ የማሳወቅ፤
4. መልካም የውል አፈጻፀም ገጽታ የመገንባትና በቅን ልቦና የመስራት፤
5. ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር የመስራት፣ እና
6. ሌሎችም ለመስኩ ጠቃሚ የሆኑ ተግባራትን የማከናወን ግዴታ አለበት፡፡

17. በዚህ መመሪያ ውስጥ የሚሸፈኑ የወጪ ምርቶችን የሚገዙ የውጭ አገር ገዥዎች ግዴታ

1. በዚህ መመሪያ የሚሸፈኑ ምርቶች ላይ በተገቡና በተመዘገቡ ውሎች ላይ የውጭ ሀገር ገዥዎች እንደውላቸው ሳይፈጸምላቸው ከቀረ እና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን አስተዳደራዊ እርምጃ በሚፈልጉበት ጊዜ በሚዘረጋው የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ የግንኙነት ዘዴ ወይም አሠራር ወይም በዲፕሎማሲ የግኙኝነት መስመር እንደውል አለመፈጸሙን ካረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ የማሳወቅ፤
2. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚሰጠው አቅጣጫ ተባብሮ የመስራት፣ እና
3. ለውል አፈፃፀም የውሉን ድንጋጌዎች እና ቅን ልቦና መሠረት በማድረግ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. የውል ይዘት

1. በዚህ መመሪያ የተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የሚፈጸሙ የወጪ ምርት ውል ይዘቶችን በተመለከተ ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪ አንድ የተያያዘው ሞዴል ውል ይዘት ለተዋዋይ ወገኖችና ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የውል ምዝገባን ሲያደርግ በማነጻፀሪያነት ያገለግላል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ 1 መሠረት የተዘጋጀው የውል ማነፃፀሪያ ሞዴል ውል እና የምዝገባ አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ የዚህ መመሪያ አካል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

### 19. የመተባበር ግዴታ

በዚህ መመሪያ አፈጻፀም ላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማንኛውም አካል ወይም ባለድርሻ አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

### 20. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1. በወጪ ምርቶች ላይ ከሚፈጸሙ ውሎች የሚመነጩ ወይም በሌላ በማናቸውም መልኩ የሚነጩ የፍትሐብሔር ወይም ወንጀል ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዚህ መመሪያ መሠረት የማይሰሩ ላኪዎች ላይ ተመጣጣኝ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤

   ሀ) የወጪ ምርቶች ላይ በሚደረግ የአገር ውስጥ ግብይት ከዋጋ በላይ በመግዛት የግብይት ስርዓቱን የሚያዛባ፤

   ለ) በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተመዘገበ ውልን እንደውል ሳፈጽም የቀረና ጉዳት በደረሰበት ሰው ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለአስተዳደራዊ ውሳኔ ማመልከቻ የቀረበበት ላኪ፤

   ሐ) በውጭ ገበያ ላይ የወጪ ምርቶችን ከዋጋ በታች በመሸጥ አገራዊ ጠቀሜታን የሚያሳጣና የግብይት ሥርዓቱን የሚያዛባ ላኪ፣ እና

   መ) ሌሎች በዚህ መመሪያ ላይ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ሳይጠብቁ በሚሰሩ

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

ላይ እንደጥፋቱ ክብደት ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ ከግብይት ማገድ እና የንግድ ፈቃድ እስከመሰረዝ የሚደርሱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይወስዳል።

3. በዚህ መመሪያ ላይ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ የተወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ አሳማኝ ምክንያት ሲቀርብ በበላይ አመራሩ ማስተካከያ ይደረጋል።
4. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ለአፈፃፀም በግልባጭ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀጽ 4 መሠረት በግልባጭ የተመዘገበላቸው አካላት አስተዳደራዊ እርምጃውን ተከትሎ ከተቋማቸው ተግባርና ኃላፊነት አንፃር መደረግ የሚገባውን ስለመፈጸማቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተከታትሎ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

## 21. የግብይት ሕጎች ተፈፃሚነት

በዚህ መመሪያ ላይ የተገለጸው የወጪ ምርት ውልን የማስመዝገብ ግዴታ በሌሎች በሥራ ላይ ባሉ የግብይት ሕጎች የሚጠየቁ ውልን የማስመዝገብ እና የማሳወቅ ተግባራትን እንዲሁም አጠቃላይ ግብይቱን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት አያስቀርም።

## 22. ድጋፍና ክትትል ስለማድረግ

1. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በማንኛውም ጊዜ የተመዘገቡ የሽያጭ ውሎች አፈፃፀም ላይ ድጋፍና ክትትል የማድረግ እና የምክር አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት አለበት።

2. በገዢዎች በኩል ለሚያጋጥም የውል አለመፈጸም በዲፕሎማሲያዊ መንገድ እንዲሁም ከአገራት የንግድ ምክር ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ውሉ የሚፈፀምበትን ሁኔታዎች የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት።

## 23. ቅንጅታዊ አሠራር

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተመዘገቡ ውሎችን፣ የምዝገባ ማሻሻዎችን እና ማቋረጫዎችን እንዲሁም ከውል አፈፃፀምና የገበያን ዋጋ ከማናር ጋር ተያይዞ የሚወስዳቸውን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ለሚመለከታቸው የወጪ ንግድ ባለድርሻ አካላት ያሳውቃል። አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል።

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መ ዝ ገ ብ ቤ ት

## 24. ስለቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓትና ውሳኔ አሰጣጥ

1. አገልግሎት ተቀባዩ በአገልግሎት አሠጣጡ ቅሬታ ካለው አስቀድሞ ለአገልግሎት ሰጪው ባለሙያ ቅሬታውን ያቀርባል፤ በባለሙያው ደረጃ ቅሬታው በአግባቡ ካልፈታለት ወይም አሳማኝ ምክንያት ካላቀረበለት በየደረጃ ለሚገኙ ለቅርብ ኃላፊዎች ቅሬታውን በጽሑፍ ያቀርባል፡፡
2. በየደረጃው በሚገኙ የቅርብ ኃላፊዎች በቂ ምላሽ ያላገኘ አገልግሎት ተቀባይ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቅሬታ አስተናጋጅ ክፍል በጽሑፍ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት አግባብ በየደረጃው ቅሬታው ካልተፈታ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች ቅሬታውን በጽሁፍ ያቀርባል፡፡ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቅሬታው ካልተፈታ ቅሬታውን በሕግ አግባብ መጠየቅ ይችላል፡፡
3. በዚህ መመሪያ መሠረት በአገልግሎት አሠጣጥ ላይ ወይም በተወሰደ አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ የሚቀርብ ቅሬታ አገልግሎት ተቀባዩ ቅር የተሰኘበት ድርጊት ከተፈጸመ ወይም አስተዳደራዊ እርምጃው ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ካልቀረበ ቅሬታው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
4. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 3 መሠረት የቀረበው ቅሬታ በደረሰው በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው ውሳኔውን በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

## 25. ስለይግባኝ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 24 መሠረት ቅሬታውን ያቀረበና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወይም በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ ካልሰጠ፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውሳኔውን እንደጸና ተቆጥሮ ቅሬታ አቅራቢ የሆነ ማንኛውም ሰው ጉዳዩን ለማየት በሕግ ስልጣን ላለው መደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት የሚኖረው ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቅሬታውን ካቀረበና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሊወስንበት ከሚገባው 10 የስራ ቀናት በኋላ ባሉት ሁለት ወራት ጊዜ ሲቀርብ ነው፡፡

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

## 26. መመሪያ ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡ ማንኛውም ማሻሻያ ተግባራዊ የሚሆነው በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሲጸድቅ ብቻ ነው፡፡

## 27. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ፈትለወርቅ ገ/እግዚአብሔር
የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት